# ስለማይነገር ስጦታው

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበሉን አቋርጠን } አዝማች
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ሕያው እንድንሆን
ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

ንፋስን ገስጾ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እርሱ መጠጊያችን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሣኤ ሰላምን ለሰጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

ከሲያል እሥራት ተፈተን ነፃ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

**አዝማች**...

# አምላኬ ለእኔ

<u>አምላኬ ለእኔ ድንቅ አድርጎልኛል</u> (2X)
የአንበሳን አፍ ዘግቶ ከሞት ታድጎኛል } አዝማች...

(አምላኬ ለእኔ) አለቀለት ሲባል (አምላኬ ለእኔ) ቅጥሩ ፈራረሰ
«« ታሪኬን ለውጦ «« ሕይወቴን አደሰ
«« ምን ባደርግለት ነው «« እንዲህ የወደደኝ
«« አፈርና ትቢያ «« ብሆን አከበረኝ

አዝማች...

(አምላኬ ለእኔ) ውለታው ብዙ ነው (አምላኬ ለእኔ) ያደረገልኝ
«« ከአንበሳ መንጋጋ «« ከሞት አስጣለኝ
«« ታምሩ በእኔ ላይ «« እጅግ ስለበዛ
«« ተመስገን ልበለው «« ልሰዋ ምስጋና

አዝማች...

(አምላኬ ለእኔ) ከእንግዲህ በኋላ (አምላኬ ለእኔ) መጽናኛ አገኘሁ
«« የጠላቴን ሴራ «« ቅጥሩን አፈረሰው
«« ከአዕምሮ በላይ ነው «« ድንቅ አድርጎልኛል
«« በመስቀል ተሰቅሎ «« ሕይወትን ሰጥቶኛል

አዝማች...

# የፀድቅ በር ነሽ

የፀድቅ በር ነሽ የሙሴ ጽላት
አክሊለ ሰማዕታት ምራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንፁሕ አክሊላችን
<u>ሐመልማለ ሲና እመቤታችን</u> (2X) } **አዝማች...**

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመቤታችን) | ለኛ ምርኩዝ ነሽ | (እመቤታችን) | ከለላም ሆንሽን |
| » » | የእሳት ሙዳይ | » » | እሳት ታቅፊሽ |
| » » | በብርሃን ተከበሽ | » » | ወርቅ ለበስሽ |
| » » | ከሴቶች ሁሉ | » » | አብ መረጠሽ |

**አዝማች...**

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመቤታችን) | ድንግል ሆይ ልጆችሽ | (እመቤታችን) | አንቺን ይጠሩሻል |
| » » | ስምሽን ለልጅ ልጅ | » » | ያሳስቡልሻል |
| » » | በተሰጠሽ ጸጋ | » » | በአማላጅነትሽ |
| » » | ምኅረትን አሰጪን | » » | ከመሃሪው ልጅሽ |

**አዝማች...**

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመቤታችን) | የአልታረሰች እርሻ | (እመቤታችን) | ዘር ያልተዘራባት |
| » » | የሕይወትን ፍሬ | » » | ሰጠችን የኛ እናት |
| » » | የታረደው መሲህ | » » | እናቱን ወደዳት |
| » » | በቀኙ ቆማለች | » » | ድንግል እመቤት ናት |

**አዝማች...**

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመቤታችን) | የእውነት ደመና | (እመቤታችን) | ዝናብ የታየባት |
| » » | ወዳናለች ድንግል | » » | የታተመች ገነት |
| » » | ክብር ለሆነችው | » » | ኑ እንዘምርላት |
| » » | ደስ ይበልሽ እንበል | » » | ለብርሃን እናት |

**አዝማች...**

# ስለረዳሽኝ እመቤቴ አወድስሻለሁ

ስለረዳሽኝ እመቤቴ አወድስሻለሁ
ከእኔ ጋር ስለሆንሽ እመቤቴ አወድስሻለሁ
ምስጋናሽን ይዤ ጠዋት ማታ ፊትሽ እቆማለሁ
ምስጋናሽን ይዤ እመቤቴ ፊትሽ እቆማለሁ
} **አዝማች…**

ኃዘን ትካዜዬ በአንቺ ተወግዷል
ልመና ጸሎቴ ሐሳቤ ተሟልቷል
ያጣሁትን ሁሉ አግቼብሻለሁ
በእናትነትሽ ዘወትር እመካለሁ

**አዝማች…**

በአንቺ ደስ ይለኛል ያርፋል ልቦናዬ
ሰላሊ ለነ ብዬ ተቃና ጉዞዬ
አልፈራም እንግዲህ ገደል እንቅፋቱን
ይዘሽኛልና ድንግል አዛኝቱ

**አዝማች…**

የተስፋ መብራቴ አትጠፊም ከፊቴ
መድሃኒቴ አንቺ ነሽ ለብቸኝነቴ
ይህች ዓለም ብትከፋ ፊቷን ብትመልስ
ጨክነሽ አታውቂም እናቴ በእኔስ

**አዝማች…**

ምስክር አልሻም ከእንግዲህ በኋላ
ነፍሴ ትጮሃለች አማላጄ ብላ
አወድስሻለሁ እናቴ እመቤቴ
በኑሮዬ ሁሉ እስከ ዕለተ ሞቴ

**አዝማች…**

# ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም (2X)
እናቱ ነሽና የመድኃኔዓለም (2X)

የሲና ልምላሜ .... ድንግል መሰላል ነሽ ....
የፍጥረታት ጌታ .... በአንቺ ያደረብሽ ....
ከአንቺ ተዋኀዶ .... እኛን ሊያድን ልጅሽ ....

አዝማች...

ምርኩዜ ልበልሽ .... ጥላ ከለላዬ ....
ጋሻዬ ነሽ አንቺ .... ለእኔ መመኪያዬ ....
በዓለም እንዳልጠፋ .... ሕይወቴ መሮብኝ ....
እንደ ወይን አጣፍጪው .... ድንግል ድረሽልኝ ....

አዝማች...

እነኋት እናትህ .... ብሎ የሰጠውን ....
በመስቀል ላይ ሳለ .... ቃል የገባለትን ....
ዛሬም ለእኛ ሰጠን .... ንፅህት ቅድስትን ....
ብለን እንድንላት .... ከልጅሽ አማልጅን ....

አዝማች...

# ላፈቀረኝ አምላክ

ላፈቀረኝ አምላክ ሁሌ እዘምራለሁ
የማዳኑን ጥበብ በአይኔ አይቻለሁ
የእኔ የቤቴ ራስ እግዚአብሔር ሆኗል
በምስኪኗ ጎጆ በረከት ሞልተሃል
} አዝማች...

ምኔን አይተኸኝ ነው እንዲህ የወደድከኝ
ሞቴን ሞተህልኝ ለክብር ያበቃኸኝ
ምስኪኑን አንስተህ ሞገስ የሰጠኸኝ
የድንግል ማርያም ልጅ አምላክ ክበርልኝ

አዝማች...

የሕይወትን ውሃ አጠጥተኸኛል
ቸርነትህንም ለእኔ አርገህልኛል
ከዓለም ጉድጓድ ውስጥ አንተ አወጣኸኝ
ተመስገን ልበልህ ሌላ ምን ቃል አለኝ

አዝማች...

ልቤ በመደነቅ ተሞላ በሥራው
የሕይወቴን ንጉሥ እንዴት ላመስግነው
ፈታኙን አድርጎ ትቢያና ገለባ
ረዳኝ አምላኬ ከቤቱ እንድገባ

አዝማች...

ጩኸቴን አድምጠህ ዳነ ስብራቴ
ሰላምን አጸናህ ለትንሿ ቤቴ
ዛሬስ ተምሬአለሁ እንደማይተው ጌታ
ስሰዋልህ ልኑር ዝማሬና እልልታ

አዝማች...

# የሥላሴን መንበር

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩብ በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት
አዕላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን አባት

} **አዝማች...**

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት
ካህናተ ሰማይ ሥሉስ ቅዱስ ሲሉ
ይህን ቅዱስ ክብር ሊያዩ የታደሉ
<u>በጽድቅ ሥራቸው በምድር ይታያሉ</u> (2X)

**አዝማች...**

የቅዱሳን ኅብረት የቅዱሳን አገር
ሲወደስ ይኖራል የሥላሴ ክብር
ጽድቅ እና ርኅራኄ የተሞላ ሰማይ
<u>እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤው እንድናይ</u> (2X)

**አዝማች...**

# በፍቅር ተስቦ

በፍቅር ተስቦ ወረደ ለእኛ ሲል
የፍቅሩን ፍጻሜ ገለጸ በመስቀል
ለእኛ ያላረገው ከቶ ምን አለና
አፋችን ዝም አይበል እናቅርብ ምስጋና } አዝማች...

(ደስ ይበለን) ሰማያትን ቀዶ (ደስ ይበለን) ታላቁ አባታችን
»» የዘመናት ንጉሥ »» ኢየሱስ ጌታችን
»» የኤፍራታው ሕፃን »» በዳዊት ከተማ
»» ተወልዶ ማደሩን »» ምሥራች ተሰማ

አዝማች...

(እንዳንተ ያለ) በኃጢአት ውስጥ ወድቀን (እንዳንተ ያለ) ስንኖር ጎስቁለን
»» አምላክ የእኔ ጌታ »» ከሞት ውስጥ አዳንከን
»» ዝናውንም አውሩ »» ለአሕዛብ ሁሉ
»» እንደ እግዚአብሔር ያለ »» ማንም የለ በሉ

አዝማች...

(ደስ ይበለን) ወረደ ወደ ምድር (ደስ ይበለን) ሰላሙን ሊሰጠን
»» ሰላም ለእናንተ ይሁን »» ብሎ እንዲሰብክልን
»» በመስቀል ተሰቅሎ »» እኛን የተቤዠን
»» ከሲኦል እሥራት »» በፍቅሩ የፈታን

አዝማች...

(ሃሌሉያ) ምስጋና በሰማይ (ሃሌሉያ) ምስጋና በምድር
»» ሁሉን ቻይ ለሆነ »» ለቸሩ እግዚአብሔር
»» ሃሌሉያ ለእርሱ »» ለነፍሳችን ጌታ
»» ዝማሬን እናቅርብ »» ከጠዋት እስከ ማታ

አዝማች...

# እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀን መሸሸጊያ ነው } **አዝማች…**

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሦብን ሳለ በኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራው ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው (2X)

**አዝማች…**

አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነዓን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት
እንደምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት (2X)

**አዝማች…**

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ (2X)

**አዝማች…**

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቄን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ (2X)

**አዝማች…**

# ገዳመ ቆሮንጦስ

ገዳመ ቆሮንጦስ የትምህርት ቦታ
የዓለሙ ንጉሥ በአንቺ ተንገላታ

አርባ ቀንና ሌሊት ክርስቶስ የጾመው
ከአጠፋነው በደል ሊያድነን እኮ ነው
መሪያችን ኢየሱስ መሆኑን ካወቅን
ጾምና ፀሎትን ማነው የከለከለን

ገዳመ ቆሮንጦስ የትምህርት ቦታ
በአንቺ ተፈተነ መምህርና ጌታ
ጌታዬ ፈታኝህ አንተ ያሳፈርከው
ይፈታተናል ዛሬም ከእኛ ጋር ነው

ላቡና ደሙ እንደ ውሃ ወረደ
በአማኑኤል ኃይል ንስሐችን ነጎደ
የዓለሙ ንጉሥ በደለኛ መስሎ
ሕይወቱን ሰጥቶናል ስለእኛ ተሰቅሎ

# የሚረዳኝ

የሚረዳኝ ሚካኤል መጣ (2X)
ታላቁን ዘንዶ ደርሶ ሊቀጣ

የኢጥቢያውን ኮከብ ዘንዶውን ተዋግቶ
ሲያጽናናኝ ይኖራል እጆቹን ዘርግቶ
ሞቴን ወደ ሠርጌ ለውጠህልኛል
ሚካኤል ወዳጄ በአንተ ደስ ይለኛል

የሚረዳኝ ገብርኤል መጣ (2X)
ከእሳቱ ባሕር እኛን ሊያወጣ

ወላፈኑ የለም ጠፍቷል ነበልባሉ
መሐላችን ቆሟል ገብርኤል ኃያሉ
የአንበሳው መንጋጋ ኃይሉን አጥቷል ዛሬ
ከጥልቁ ተሰማ የአርያም ዝማሬ

የሚረዳኝ ሩፋኤል መጣ (2X)
ከእሳቱ ባሕር እኛን ሊያወጣ

የጠላቴ ምሽግ ግንቡ ፈራረሰ
በሩፋኤል ፀበል ጉልበቴ ታደሰ
ስብራቴ ድኖ ከደጁ ቆሜአለሁ
ዛሬ ሙሉ ሰው ነኝ እዘምርለታለሁ

የሚረዳኝ ኡራኤል መጣ (2X)
የጥበብ ጽዋ እኔን ሊያጠጣ

የጨበጥከው ጽዋ ከንፈሬን ቢነካኝ
በጥበብ ተሞላሁ ዘምር ዘምር አለኝ
የፍቅር መልአክ ነህ የሰው ልጆች ጥላ
ኡራኤል ረዳቴ የነፍሴ ከለላ

# ባለውለታዬ

ባለውለታዬ ባለውለታዬ
ከአመድ ያነሳኸኝ ከትቢያ ተጥዬ } አዝማች…
ተመስገን ጌታዬ

በሩን ቢዘጋብኝ ስምዖን ጨክኖ
ዝቅ አድርጎ ቢያየኝ ከአይሁድ ጋር ሆኖ
እንድቀርብ ወደ እርሱ አዘዘ ጌታዬ
እግሩን አጥበዋለሁ ወድቄ በእንባዬ (2X)

አዝማች…

የቀራጭ አለቃ ቢሆንም ሥራዬ
እንድወርድ ከዛፉ አዘዘ ጌታዬ
ማዕረጌን መሸከም እስኪያቅተኝ ድረስ
ቤቴ ተባረከ በኢየሱስ ክርስቶስ (2X)

አዝማች…

ድንጋይ የጨበጡ ፈራጆች ከበውኝ
ነውሬን ዘርዝረው ጌታ ፊት አቆሙኝ
ፈረደችባቸው ኃጢአትም በእነሱ
በሰላም ሂጅ ብሎ ምሮኛል ንጉሡ (2X)

አዝማች…

የማምነውን አምላክ አውቀዋለሁ እኔ
በሰራልኝ ሥራ በዕድሜ በዘመኔ
ፍቅሩን ተሸክሟል የልቤ ትከሻ
ልለየው አልችልም እስከ መጨረሻ (2X)

አዝማች…

# እግዚአብሔር እረኛዬ ነው

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝ የለም
በጠላት ፊት ሞገስ የሆነኝ እንደ አንተ የለም
የእኔን ሕይወት በረከት ሞልተህ ከፍ ያደረግከኝ
አማኑኤል ይክበር ይመስገን ለዚህ ያበቃኝ
} አዝማች...

ያለ አንተ የሆነ ምን አለ ጌታዬ
ሁሉም በአንተ ሆኗል ይድረስ ምስጋናዬ
ጎዶሎው ሞልቶልኝ ከሰው መለካቴ
ለክብር የበቃሁት በአንተ ነው አባቴ

አዝማች...

ሞቴን ስጠባበቅ ነገ ዛሬ እያልኩኝ
አዳም ተምረሃል የሚል ቃል ሰማሁኝ
ሞትን ሲፈርዱበት ይግባኝ አልጠየቀም
የእኔን ሞት ሞተልኝ አምላክ መድኃኔዓለም

አዝማች...

ከገናናው ንጉሥ ከፈርዖን ቀንበር
ማነው የሚያወጣን ብለን ስንሸበር
ለካስ የማይተወን እግዚአብሔር አለልን
ሙሴን አስነስቶ ሕዝቦቹን ታደገን

አዝማች...

ምናምንቴ ብሎ ጎልያድ ቢንቀኝ
የተማመንኩበት ስምህ ግርማ ሆነኝ
በውሃ ውስጥ ስጓዝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው
እረኛዬ ለእኔ የጸና ግንብ ነው

አዝማች...

# አልተወኝም ጌታ

አልተወኝም ጌታ ለካስ ይወደኛል (2X)
ዛሬም ስበድለው ልጄ ነህ ይለኛል (2X) } አዝማች...

ተሸሸግሁኝ ከእርሱ በኃጢአት ጫካ
ብጠፋበት እንኳን አልተወኝም ለካ
ዛሬም ልጄ ብሎ ዳግም ይጠራኛል
ለካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል (2X)

አዝማች...

ለሥልጣን ለክብሬ ብዬ ስክደው
ለገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው
ለእኔ ያለውን ፍቅር አልቀነሰብኝም
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም (2X)

አዝማች...

ታዲያ ለዚህ ክብሩ ለሌለው ወሰን
ከድጥ አፈር አመድ ላወጣኝ እኔን
በሕይወቴ ሁሉ ፍጹም ለመራኝ
ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ (2X)

አዝማች...

# ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና

ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና
እግዚአብሔር ይመስገን (2X) } አዝማች...

(ምሕረቱ) ዓይኖቼን ከእንባ ከኃዘን ታድጓል
«« በዘመኔ ሁሉ መጽናናት ሆኖኛል
«« ከቁጥርም በዝቷል ከአእምሮ በላይ ነው
«« ዘመን የማይሽረው ዘለዓለማዊ ነው

አዝማች...

(ምሕረቱ) ከነገሥታት ማዕድ እድል ፈንታን ሰጠኝ
«« ከተረሳሁበት እኔን አስታወሰኝ
«« ትንሿን ጸሎቴን ከትጋት ቆጥሮልኝ
«« ከሰላሙ መንደር ከነዓን አገባኝ

አዝማች...

(ምሕረቱ) ይታደጋል ከሞት በጥልቅ ለተጣሉ
«« ምሥራች ይሆናል በሞት ጥላ ላሉ
«« የኃጢአትን ክምር ከላያችን ንዶ
«« ደስታን ያለብሰናል ማቃችንን ቀዶ

አዝማች...

(ምሕረቱ) ለጠላት ዘለፋ እኛን መቼ ተወን
«« በደልን ደምስሶ ልጆቹ አደረገን
«« እስከ ሸበት ድረስ እስከ ሽምግልና
«« በዘመኔ ሁሉ ይረዳኛል ገና

አዝማች...

# ሞታችንን ሞተ

ሞታችንን ሞተ በመስቀል ታግሶ
ጽድቅን አስተማረን በጽድቅ ተመላልሶ
የሠራዊት ጌታ መድኃኔዓለም
በመስቀል ላይ ዋለ በኢየሩሳሌም (2X)
} አዝማች...

በርባን እኔ ነበርኩ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
ክፉ ወንበዴው መድኃኔዓለም
በመስቀል ላይ ሆኖ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
ሞቴን ወሰደው መድኃኔዓለም

አዝማች...

ኃጢአት ሞትን ወልዳ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
ሞት ቢያመጣብን መድኃኔዓለም
ጽድቃችን ተገልጦ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
ሕይወት ለገሰን መድኃኔዓለም

አዝማች...

እጆቹ ታሰሩ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
እስረኛ ሊፈታ መድኃኔዓለም
በመቃብር ያለው (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
የሞት ኃይል ተረታ መድኃኔዓለም

አዝማች...

ራቁቱን ሆኖ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
እኛን አለበሰ መድኃኔዓለም
ሕይወታችን ሆኖ (መድኃኔዓለም መድኃኔዓለም)
በመስቀል ነገሰ መድኃኔዓለም

አዝማች...

# አንተ ስትናገር

አንተ ስትናገር እኔ እንድሰማ
እንደ ሊድያ ልቤን ክፈትና
ወደ ልቤ ግባ እባክህ ጌታዬ
በእምነቴ እንድፀና ባርክልኝ ሕይወቴን

**አዝማች…**

ጆሮዬን ክፈት ደንቁሯል በዓለም
በሥጋ ተዘግቶ ቃልህን አይሰማውም
የማልኮስን ጆሮ እንደቀጠልክለት
የልቤንም ጆሮ ጌታ ክፈትልኝ

**አዝማች…**

አንተ ስታስተምር በሥጋ ቁጭ ብዬ
ሐሳቤ ተከፍሎ በእንቅልፍ ተታልዬ
እንደ ዛለው ወጣት ከደርቡ ላይ እንዳልወድቅ
በማስተዋል መንፈስ ካንተ ጋር ልታረቅ

**አዝማች…**

ሥጋ በመንፈስ ላይ ሰልጥኖ እንዳይጥለኝ
በመንፈስ አስተምረኝ ይኸው ከእግርህ ሥር ነኝ
በቃልህ ልመራ መንገድህን ልወቅ
በእውነተኛ ፍቅር ካንተ ጋር ልታረቅ

**አዝማች…**

ቃልህ በሕይወቴ በእምነት ተዋህዶኝ
ከአንተ የተቀበልኩት ኩልህ አጥርቶልኝ
አንተን እጠብቃለሁ ጌታ ሆይ ቶሎ ና
ያችን ጽዮን አገር ናፍቄአለሁና

**አዝማች…**

# በኃጢአት ያደፈ

በኃጢአት ያደፈ ሆኗል ሰውነቴ
አብቂኝ ለንስሐ አማልጂኝ እናቴ } **አዝማች…**

(በኃጢአት ያደፈ) በኃጢአቴ ብዛት (በኃጢአት ያደፈ) ልቤ ሲታወር
«« ተብትቦ ሳይጥለኝ «« የኃጢአቴ ድር
«« በጣጥሰሽ ጣይልኝ «« የኃጢአትን ወጥመድ
«« ድንግል ሆይ አማልጂኝ «« አርቂኝ ከዚህ ጉድ

**አዝማች…**

(በኃጢአት ያደፈ) መቆም አቅቶኛል (በኃጢአት ያደፈ) በደሌ በዝቶብኝ
«« እማጸንሻለሁ «« ልመናዬን ስሚኝ
«« ኃጢአቴን መሸከም «« እኔ አልቻልኩምና
«« እናቴ ሆይ ስሚኝ «« ድንግል በጥሞና

**አዝማች…**

# ኃይልን በሚሰጠኝ

ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ (2X)
መከራ ቢገጥመኝ ለበጎ ነው ብዬ አልፋለሁ
ፈተና ቢገጥመኝ ለበጎ ነው ብዬ አልፋለሁ
} አዝማች (2X)

በሰንሰለት አስረው በወህኒ ቢጥሉኝ
መከራን አብዝተው እጅግ ቢያስጨንቁኝ
ለበጎ ነው ብዬ ተስፋ አድርጌሃለሁ
ይሁን አንተ ያልከው እገዛልሃለሁ

አዝማች...

ትናንትናም ዛሬም አንተ ያው አንተ ነህ
ፍቅርህ አይቀየር ወረትም የለብህ
ስምህን መጥራቴ ሞገስ ሆኖልኛል
ጠላቴ ቢፎክር መቼ ያሸንፈኛል

አዝማች...

በመከራው ጽናት ጉልበቴ ደከመ
ጥቃቴ ከቦኛል ተስፋዬም ጨለመ
ነገር ቢሆን ባይሆን አንተን እንዳከብር
አድለኝ በፀጋህ ጌታ በአንተ ፍቅር

አዝማች...

ከሀገር ወጥቼ በዱር መሰደዴ
ከባዕዳን አገር ርቄ መሄዴ
ለበጎ ነውና መቼ ይከፋኛል
ፈጽሞ እንዳልጠፋ ክንድህ ይይዘኛል

አዝማች...

ትናንትናም ዛሬም አንተ ያው አንተ ነህ
ፍቅርህ አይቀየር ወረትም የለብህ
ስምህን መጥራቴ ሞገስ ሆኖልኛል
ጠላቴ ቢፎክር መቼ ያሸንፈኛል

አዝማች... (2X)

# የብርሃን ጎርፍ

የብርሃን ጎርፍ ናት ድንግል እናታችን
ከሰማይ እያበራች ደስ አለው ልባችን
ፍቅርሽም ሰላምሽም ድኅነት ይሁነን ኦ ኦ
ፍጥረት በሙሉ በሙሉ ፊትሽ ይወድቃሉ
ጸጋሽ ይድረሰን ይድረሰን ይሰጠን እያሉ

**አዝማች…**

የእኔ ልብ ምን ጽድቅ አለው አንቺን ለማስተናገድ
የኃጢአት ጐተራ ነው የተሞላ በስስት
ኧረ እንዴት? ኧረ እንዴት? ድንግል ትኑርበት ኦኦ
አትጸየፍም የኔን ልብ ታሰናዳዋለች
ስለ ኃጢአቴ የኔ እናት ምልጃ ታቀርባለች

**አዝማች…**

ልባቸውን የዘጉ ድንግልን ለማስገባት
ሕሊናቸው ይመለስ እንጸልይ በዚህ ጥፋት
አምላክን ይዛ ነው ድንግል የምትመጣው
እሷን ስንመልስ ጌታን ነው የምናስቀይመው

**አዝማች…**